# ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# የቅርስ ጥናትና ምርምር ፈቃድ

# አሰጣጥ መመሪያ

## ቁጥር 485/2013

ታህሣሥ 2006 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# መመሪያ ቁጥር 485/2013
# የባህልና ቱሪዝም
# ሚኒስቴር
# የቅርስ ጥናትና ምርምር ፈቃድ አሰጣጥ
# መመሪያ

ቅርሶች የማንነት መገለጫ ብቻ ሳይሆኑ ያለፈው ትውልድ የታሪክና የሥልጣኔ አሻራ፤ የአሁኑ ትውልድ የልማትና የብልጽግና መገለጫ፤ የተተኪው ትውልድ ደግሞ አለኝታና ተስፋ እንዲሁም ለሀገሪቱ የሀብትና የልማት መሠረት ስለሆኑ፤

በአገሪቱ በምድርና በከርሰ ምድር ውስጥ የሚገኙ ቅርሶች ላይ፣ በብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ላይ ብሎም በተለያየ ምክንያት ከአገር የወጡ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ላይ የሚደረጉ ዘርፈ ብft የጥናትና ምርምር ስራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል ለአገር ልማት የሚውሉበት መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የቅርስ ጥናትና ምርምር በተጠና ስርዓትና ግልፅነት ባለው አሰራር መከናወን ስላለበት እና የሀገርቷንና የዜጎቿን መብትና ጥቅም በሚያስጠብቅ መልክ እንዲከናወን ማድረግ ስለሚገባ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 32 እና አንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1) **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የቅርስ ጥናትና ምርምር ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 485/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2) **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

1. "አዋጅ" ማለት የቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 ነው፡፡

2. በአዋጁ አንቀፅ 3 የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

3. "የቅርስ ጥናትና ምርምር" ማለት ቅርሶችን ለመፈለግ፣ ለማግኘት፣ ለመለየት፣ ዶክመንት ለማድረግ፣ እና ለሕትመት ለማብቃት የሚደረግ ጥናት ወይም ምርምር ነው፡፡

4. "ተመራማሪ" ማለት በግሉ ወይም በአንድ የተመራማሪዎች ቡድን ውስጥ ታቅፎ በሰለጠነበት የሞያ ዘርፍ ምርምር የሚያካሂድ ባለሞያ ነው፡፡

5. "የፓሊዮአንቶሎጂ ጥናት"ማለት በስነ-ህይወት ዘርፍ የሚካሄድ ጥናትና ምርምር ነው፡፡

6. "የፓሊዩአንትሮፖሎጂ ጥናት" ማለት በቅድመ ዘመን የስነ-ሰብ ጥናት የሚያካሄድ የጥናትና ምርምር ዘርፍ ነው፡፡

7. "የአርኪዎሎጂ ጥናት" ማለት የሰውን ልጅ የቅድመ ታሪክና የታሪክ ዘመን የሚያጠና ዘርፍ ነው፡፡

8. "የአንትሮፖሎጂ ጥናት" ማለት የስነ-ሰብ ጥናትና ምርምር ዘርፍ ነው፡፡

9. "ቡድን" ማለት ሁለትና ከዛ በላይ አባላት ያሉት የጥናትና ምርምር የባለሙያዎች ስብስብ ነው፡፡

10. "የቡድን መሪ" ማለት በአንድ የተመራማሪዎች ቡድን የሚካሄድን የቅርስ ጥናትና ምርምር ተግባር በበላይነት የሚመራ ባለሞያ ነው፡፡

11. "የጥናትና ምርምር ፈቃድ" ማለት በመስክ በአንትሮፖሎጂ፣ በአርኪዎሎጂ በፓሊዩአንትሮፖሎጂ ወይም በፓሊዮአንቶሎጂ ዘርፍ ለማጥናት ላመለከተ ተመራማሪ ወይም ቡድን በጽሑፍ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

12. "የቅርስ አድን ፈቃድ" ማለት በግንባታና ሌሎች የመሠረተ ልማት ማስፋፋት ሥራ ምክንያት ወይም በተፈጥሮ ክስተቶች ለአደጋ የተጋለጡ ቅርሶችን በአፋጣኝ ለማዳን የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

13. "ድህረ ምረቃ ጥናት ፈቃድ" ማለት ለኢትዮጵያዊያንና ለውጪ ተማሪዎች ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ የሚሆን በኢትዮጵያ ቅርሶች ላይ ጥናት እንዲያደርጉ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

14. "የጥናት ቦታ ወሰን" ማለት ለአንድ ተመራማሪ ወይም የምርምር ቡድን ጥናት እንዲያካሂድ የሚፈቀድ የቦታ መጠነ ሥፋት ልክ ነው፡፡

15. "የጥናትና ምርምር ውጤት ሕትመት" ማለት ስለ ቅርሶች ግኝትና ጥናት በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግል የሚችል መረጃ የያዘ፣ ተገምግመው በሚታተሙ ሳይንሳዊ መጽሔቶች፣ በሞኖግራፍ፣ በመጻሕፍትና በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች ላይ የሚወጣ ጥናታዊ ጽሑፍ ወይም አጠቃላይ የቅርሶችን አገኛኘት፣ ይዘትና ዝርዝር ጥናት የሚያካትት ህትመት ማለት ነው፡፡

16. "የጥናትና የምርምር ፈቃድ ዘመን" ማለት በቅርሶች ላይ እንደ ምርምር ዘርፉ ዓይነትና ስፋት ምርምር ለማድረግ ለሦስት ዓመት ጊዜ ለአንድ ተመራማሪ ወይም የምርምር ቡድን የሚሰጥ የጥናት ፈቃድ ዘመን ነው፡፡

17. "የፈቃድ ዓመት" ማለት ለአንድ ተመራማሪ ወይም የምርምር ቡድን በፍቃድ ዘመን ውስጥ በየዓመቱ የሚታደስ ሆኖ ለአንድ ዓመት የሚሰጥ የፈቃድ ጊዜ ነው፡፡

18. "ማመልከቻ" ማለት ጥናትና ምርምር የማድረግ ፈቃድ ለማግኘት ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ ማመልከቻ ነው፡፡

19."ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬደዋ መስተዳድርን ይጨምራል፤

20. “ቢሮ“ ማለት በክልሎች ውስጥ በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚሰራ አስፈፃሚ አካል ነው፡፡

21.“ሚኒስቴር” ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው::

22.“ባለስልጣን”ማለት የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡

23.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል

3) <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በሀገሪቱ በሚደረጉ የቅርስ ጥናትና ምርምር ስራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የጥናትና ምርምር ዘርፎች፤ የፈቃድ ማመልከቻ ይዘትና መስፈርቶች</u>

4) <u>ፈቃድ የሚሰጥባቸው የቅርስ ጥናትና ምርምር ዘርፎች</u>

1. የፓሊዮአንቶሎጂ ጥናትና ምርምር
2. የፓሊዮ-አንትሮፖሎጂ ጥናትና ምርምር
3. የአርኪዎሎጂ ጥናትና ምርምር
4. የአንትሮፖሎጂ ጥናትና ምርምር

5) <u>ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ልዩ ልዩ ተግባራት</u>

1. የቅርስ አድን ፈቃድ

2. በመስክ ላይ የሚደረግ የቅርስ ጥናትና ምርምር ስልጠና

3 በመስክ ላይ የሚገኙ ተንቀሳቃሽና የቋሚ ቅርሶች ጥናት

6) <u>ስለጥናትና ምርምር ማመልከቻ ይዘት</u>

ማንኛውም የጥናትና ምርምር ፍቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡፡

1. የተመራማሪውን ወይም የቡድን መሪውን ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣የፓስፖርት ኮፒ
2. በጥናት ውስጥ የሚሳተፉ የቡድን አባላት ስም ዝርዝር፤
3. የሰለጠኑበት የሙያ ዘርፍና የትምህርት ደረጃቸውን የሚያመላክት ማስረጃ ኮፒ፣
4. የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ (ሲቪ)፣
5. የሚሰሩበት ወይም የሚማሩበት ተቋም ስምና ሙሉ አድራሻ እንዲሁም የተቋሙ የድጋፍ ደብዳቤ፣
6. ስለ ቡድን መሪው /መሪዎች/ ምሥክርነት ሊሰጡ የሚችሉ ጥናቱ በሚካሄድበት ዘርፍ በምርምር ሥራዎቻቸው የታወቁ ሦስት ባለሙያዎች ስምና ሙሉ አድራሻ፣
7. የጥናቱ ርዕስ፣
8. የጥናቱ መስክ፣
9. ጥናቱ የሚፈጀው ጊዜ፣
10. የመስክ ጥናቱ የሚከናወንበት ጊዜ (ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት) ፣
11. ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ የቦታው ልዩ መጠሪያ፣
12. ጥናቱ የሚካሄድበት ሥፍራ መጠን /የቦታ ሥፋት/ በኢትዮጵያ የካርታ ሥራ ኤጀንሲ በ1፡50,000 መጠን የተዘጋጀ ቶፖግራፊክ ካርታ እና ከሳተላይት የተነሱ ምስሎች፣
13. በጥናቱ ሂደት የሚመለሱ ዋና ዋና ጥያቄዎችና መላምቶች፣
14. የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚጠቀምባቸው የጥናት ሥልቶች፣
15. ጥናቱን ለማካሄድ በመስክ የሚገለገልባቸውን ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች፣
16. ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠንና ምንጭ፣
17. ጥናቱን ለማካሄድ የገንዘብ ድጋፍ የተጠየቀበት ፕሮፖዛል ኮፒ፣ እና
18. የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጠው ድርጅት /ተቋም ገንዘቡን መስጠቱንና የተገኘውን ገንዘብ መጠን፡፡

7) ***የጥናትና ምርምር ጥያቄ አቀራረብና ሂደት***

1. አንድ ተመራማሪ ወይም ftድን ለመጀመሪያ ጊዜ የጥናትና የምርምር ጥያቄ ሲያቀርብ ስለሚያጠናው ጉዳይ ከአንድ ገጽ ያልበለጠ ፍሬ ጉዳዩን የሚያመለክት ጥያቄ ወደ መስክ ለመሄድ ከታቀደው ጊዜ ሁለት ወር ቀደም ብሎ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይጠበቅበታል፣
2. ባለሥልጣኑ የጥናቱን አስፈላጊነት በመገምገምና ለጥናት የተጠየቀው ቦታ ከዚህ ቀደም በሌሎች ተመራማሪዎች ያልተያዘ መሆኑን በማረጋገጥ አንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀስ 1 የቀረበው የጥናትና ምርምር ፈቃድ ጥያቄ ተቀባይነት ሲያገኝ የጥናትና ምርምር ፈቃድ የማመልከቻ፣ እና የጥናትና ምርምሩን ክፍያ፣ በብሔራዊ ባንክ በኩል ለባለስልጣኑ ክፍያ ይፈፀማል፤
4. አመልካቹ የጥናትና ምርምር ማመልከቻ ክፍያ መክፈሉ ሲረጋገጥ የጥናት መጠየቂያ ቅጹ እንዲሰጠው ይደረጋል፣
5. ማንኛውም ተመራማሪ ወይም ftድን በፍቃድ ማመልከቻው ቅጽ ላይ የሚሞላቸው መረጃዎችና ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው የሚቀርft ማናቸውም ማስረጃዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፉና ጽሑፎቹም የተተየft መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
6. የጥናት ፈቃድ ጠያቂው በዚህ አንቀፅ የተጠቀሱትን ካሟላ፤ ቅጹንና ክፍያ የፈጸመበትን ደረሰኝ ወይም የሚመለከተውን የድጋፍ ደብዳቤ ከአስፈላጊው መረጃዎች ጋር በማያያዝ ለባለስልጣኑ ገቢ ያደርጋል፣
7. በቂና አሳማኝ ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር ለአንድ የጥናት ዓመት የተከፈለ የማመልከቻም ሆነ የጥናትና ምርምር ክፍያ የሚያገለግለው ጥናቱ ይካሄዳል ተብሎ ለተጠየቀበት ዓመት ብቻ ነው፡፡

8) ***የአርኪዎሎጂ፣ የፓሊዮንቶሎጂና የፓሊዮ-አንትሮፖሎጂ ፈቃድመስፈርቶች***

ማንኛውም ሰው በአርኪዎሎጂ፣ በፓሊዮንቶሎጂ ወይም በፓሊዮ-አንትሮፖሎጂ የጥናት መስኮች ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላትይኖርበታል፡፡

1. የጥናትና ምርምር ftድኑ መሪና አባላት የትምህርት ዝግጅትና ብቃት እንዲሁም የምርምር ልምድ ሊካሄድ ከታቀደው ጥናትና ምርምር ዓይነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው፤
2. ጥናትና ምርምሩን ለማካሄድ ያገኘውን የገንዘብ መጠን፣ የተሰጠበት የገንዘብ ዓይነት እንዲሁም ለምን ያህል ጊዜ እንደተሰጠው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ገንዘftን ካገኘበት ተቋም ማቅረብና ወደ ሀገር የሚያስገባቸውን ለጥናትና ምርምር የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ለባለሥልጣኑ ማስመዝገብ የሚችል፡፡

3. የጥናትና ምርምር ftድን መሪው የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ እና በመስኩ የሥራ ልምድ ያለው ለመሆኑ ምስክርነት ሊሰጡ የሚችሉ የመስኩ ባለሙያዎች ስምና አድራሻ ማቅረብ የሚችል፤

4. ከኢትዮጵያዊያን የftድኑ አባላት፣ ልዩ ሙያ ካላቸውና የቴክኒክ ድጋፎችን ከሚሰጡ ባለሙያዎች እና በመስኩ የፒ.ኤች.ዲ ትምህርታቸውን ከሚከታተሉ የውጭ ዜጋ ተማሪዎች በስተቀር ሌሎች የftድን አባላት ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪ ያላቸው፤

5. ከዚህ ቀደም በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሙያውን ሥነ-ምግባር የሚጻረር ሪኮርድ የሌለባቸው የftድኑ አባላት መያዝ፤

6. ለመስክ ጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ቁሶችና መሣሪያዎች ማሟላት፤

7. የሚቀርበው የጥናት ሥልት ftድኑ ካለው የጥናት መሣሪያዎችና ከአባላቱ ሙያና እውቀት ጋር የሚጣጣም መሆን፤

8. ftድኑ ጥናቱን ለማካሄድ ያገኘው የገንዘብ መጠን ከአባላቱ ብዛት፣ ከጥናቱ ዓይነት፣ በመስክ ከሚቆይበት ጊዜና ከተፈቀደለት መካነ ቅርስ ስፋት አንፃር በቂ መሆን፣›

9. የጥናትና ምርምር ftድኑ ከመስክ ለሚያሰባስባቸው ቅርሶች በቂ እና ደረጃውን የጠበቀ ማከማቻ ካቢኔቶችና መደርደሪያዎችን ማሟላት፤

10. ftድኑ ከባለስልጣኑ የሚመደftለትን ኢትዮጵያውያን የቅርስ ምርምር ባለሙያዎች በምርምር ሥራ ውስጥ የሚያሳትፍና አቅም መገንባት የሚችል፤

11. ጥናቱን በሚያካሂድበት ቦታ ለአደጋ የተጋለጡ ቅርሶች ላይ ጥንቃቄ የማድረግና የማዳን ኃላፊነት የሚወስድ፤

12. ተመራማሪው ወይም ftድኑ አዲስ የጥናት ፈቃድ ለማግኘት ጥያቄ ቢያቀርብ ቀደም ሲል በተፈቀደለት ቦታ ላይ የጀመረውን ጥናትና ምርምር ማጠናቀቁ፣ ከመስክ ላሰባሰባቸው ቅርሶች ተገቢውን እንክብካቤና ምዝገባ ማከናወኑ፣ በተሰጠው ፈቃድ መሠረት በቂ መረጃ የሚሰጡ ሳይንሳዊ ጽሑፎችን ማሳተሙ፣ የጥናትና ምርምር ሥራውን በሀገሪቱ ሕግ መሠረት ማከናወኑ እና ለባለሥልጣኑ የአቅም ግንባታ አስተዋጽኦ ማድረጉ፤

13. የፈቃድ ዘመኑን ላጠናቀቀና በአዲስ መልክ የፈቃድ ማመልከቻ የሚያቀርብ ተመራማሪ ወይም ftድን የሚስተናገደው በቅድሚያ በተሰጠው የፈቃድ ዘመን ያሳተማቸው የምርምር ሕትመት ውጤቶች ለሳይንስና ለሀገር ገጽታ ግንባታ ያበረከተው አስተዋጽኦ፣ ለኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች አቅም ግንባታ ያበረከተው ድርሻ እንዲሁም ያሰባሰባቸውን ቅርሶች ባለሥልጣኑ በሚያቀርበው ፎርማት ዶክሜንት ማድረጉና የኪዩሬሽን ሥራ በአጥጋቢ ሁኔታ ማከናወኑ፡፡

9) <u>*የአንትሮፖሎጂ ጥናት ፈቃድ መስፈርት*</u>

1. ማንኛውም የአንትሮፖሎጂ ጥናት ፍቃድ ለማግኘት የሚቀርብ አመልካች ቢያንስ የማስተርስ ዲግሪና በማመልከቻው ካቀረበው የጥናትና ምርምር ጥያቄ አኳያ ተዛማጅ የሥራ ልምድ ያለው ተመራማሪ ወይም የቲድን መሪ መያዝ ይኖርበታል፡
2. አንድ ነባር ተመራማሪ አዲስ የጥናት ቦታ ለማግኘት ጥያቄ ቢያቀርብ ፈቃድ የሚሰጠው ቀደም ሲል በተፈቀደለት ቦታ ላይ የጀመረውን ጥናትና ምርምር ማጠናቀቁ፣ ከመስክ ላሰባሰባቸው ቅርሶች ተገቢውን እንክብካቤና ምዝገባ ማከናወኑ፣ በተሰጠው ፈቃድ መሠረት በቂ መረጃ የሚሰጡ ሳይንሳዊ ጽሑፎችን ማሳተሙ፣ የጥናትና ምርምር ሥራውን በሀገሪቱ ሕግ መሠረት ማከናወኑና ለባለሥልጣኑ የአቅም ግንባታ አስተዋጽኦ ማድረጉ ተረጋግጦ ይሆናል፤
3. የፈቃድ ዘመኑን ላጠናቀቀና በአዲስ መልክ የፈቃድ ማመልከቻ የሚያቀርብ ተመራማሪ ወይም ቲድን የሚስተናገደው በቅድሚያ በተሰጠው የፈቃድ ዘመን ያሳተማቸው የምርምር ሕትመት ውጤቶች ለሳይንስና ለሀገር ገጽታ ግንባታ ያበረከተው አስተዋጽኦ፣ ለኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች አቅም ግንባታ ያበረከተው ድርሻ እንዲሁም ያሰባሰባቸውን ቅርሶች ባለሥልጣኑ በሚያቀርበው ፎርማት ዶክሜንት ማድረጉና የኪዩሬሽን ሥራ በአጥጋቢ ሁኔታ ማከናወኑ፡፡

10) <u>*ስለድህረ ምረቃ ጥናት ፈቃድ*</u>

1. የድህረ ምረቃ ጥናት ፈቃድ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡-
   ሀ. የአማካሪ መምህር ስም፣ የትምህርት ተቋም ስም፣ የሚከታተሉትን የትምህርት ዓይነት፣ የመመረቂያ ጽሑፋቸውን ርዕስ፣ የጥናቱ ስልት፣ ጥናቱ የሚፈጀው ጊዜ፣ ለጥናቱና ምርምሩ ማስኬጃ የተገኘ የገንዘብ መጠን፤
   ለ. የቀረበው የጥናት ጥያቄ ማመልከቻ አመልካቹ ከሚከታተለው የትምህርት ዘርፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑን፤
   ሐ. የተማሪው አማካሪ በመስኩ የሠለጠነና በቂ ልምድ ያካበተ መሆኑን፤፡
2. የድህረ ምረቃ ጥናት ጥያቄ አቀራረብ የሚፈፀመው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1-6 በተጠቀሰው መሠረት ይሆናል፡፡
3. የድህረ ምረቃ ጥናት የሚሰጠው የፈቃድ ጊዜ ለአራት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ተማሪው ከአቅሙ በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ጥናቱን ማቋረጡን የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ ከሚማርበት ተቋም ካቀረበ የጥናት ጊዜው ለአንድ ዓመት ሊራዘምለት ይችላል፡፡

4. ተማሪው ለጥናቱ የተፈቀደለት ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ቦታው ለአንድ ዓመት ለሌላ አጥኚ አይሰጥም፡፡ ነገር ግን የአንድ ዓመት የጊዜ ገደቡ ካበቃ በኋላ ቀጣይ ጥናት ማድረግ ቢፈልግ ተማሪው ከሌሎች አጥኚዎች ቅድሚያ ለማግኘት በቅድሚያ ማመልከት ይኖርበታል፡፡
5. በፓሊዮንቶሎጂ፣ በአርኪዎሎጂ እና በፓሊዮ አንትሮፖሎጂ የጥናት መስኮች ተማሪው በመስክ የቁፋሮ ጥናት ለማካሄድ የሚችለው አማካሪ መምህሩና የባለሥልጣኑ ተወካይ ባሉበት ብቻ ይሆናል፡፡
6. ተማሪው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 3፣ 4፣ 9፣ እና 11 ከተጠቀሱት ግዴታዎች በስተቀር ሌሎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## ግምገማና ፈቃድ አሰጣጥ

### 11) የጥናትና ምርምር ግምገማና ፈቃድ አሰጣጥ

1. ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ የተጠቀሱት የጥናትና ምርምር ማመልከቻውን ይዘትና መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ገምግሞ ውጤቱን ያሳውቃል፡፡
2. የጥናትና ምርምር ፈቃድ የአመልካቹን ስም፣ የጥናትና ምርምር ቡድኑ ስም፣ የጥናቱ ርዕስ፣ ፈቃድ የተጠየቀበትና የተሰጠበትን ቀን፣ ፈቃዱ የተሰጠበትን የጥናት መስክ፣ ጥናቱ የሚካሄድበትን ቦታ ፣ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣ ፈቃዱን የሰጠው አካል ስም ፊርማና ማህተም ይኖረዋል፡፡
3. ለግምገማ የቀረበ ማመልከቻ ያልተሟላ ሆኖ ከተገኘ ጥያቄውን ላቀረበው ተመራማሪ ወይም ቡድን መሪ መጠይቁን አሟልቶ ወይም አስተካክሎ እንዲያቀርብ በባለስልጣኑ በኩል ይገለጽለታል፡፡ ምላሽ በተሰጠው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መጠይቁን አሟልቶ ካላቀረበ ጥያቄው ይሰረዛል፡፡

### 12) በአርኪዎሎጂ፣ በፓሊዮንቶሎጂ እና ፓሊዮ አንትሮፖሎጂ የሚፈቀደው የጥናት ቦታ መጠን

1. በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1-3 ላይ ለተጠቀሱት የጥናትና ምርምር ዘርፎች ለጥናትና ምርምር የሚፈቀደው ቦታ መጠን ያልተቆራረጠ ሆኖ ከ100 ካሬ ኪሎ ሜትር ያልበለጠ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ በተጠቀሱት የጥናት መስኮች የቅድመ አሰሳ ባልተካሄደባቸው ቦታዎች አሰሳ ለማድረግ እና የጥናት ቦታ ለመምረጥ በአንድ የፈቃድ ዓመት የሚሰጠው የቦታ መጠን ከ100 ካሬ ኪሎ ሜትር ሊበልጥ ይችላል፡፡

3. የቅድመ አሰሳ ጥናት በሚከናወንበት ጊዜ የጥናት ቦታ ከመምረጥ ውጪ ምንም ዓይነት የቅርስ ማሰባሰብም ሆነ የቁፋሮ ተግባር ማከናወን አይፈቀድም፡፡ ነገር ግን የጥናት ቦታ

በሚመርጥበት ጊዜ ቅርሱ አደጋ የሚደርስበት ሆኖ ካገኘው ከባለስልጣኑ ተወካይ ጋር የተገኘውን ቅርስ በመመዝገብ ወደሚመለከተው የቅርስ ክምችት ቦታ ማምጣት ይጠበቅበታል፡፡

13) <u>ለጥናትና ምርምር የሚፈቀድ ጊዜ</u>

1. የአዋጁ አንቀጽ 33 እንደተጠበቀ ሆኖ ጥናቱ በተፈቀደው የጥናት ዘመን ውስጥ ካልተጠናቀቀ ተመራማሪው የጥናት ጊዜው እንዲራዘምለት ማመልከቻ ሲያቀርብ በቅድሚያ በሰራበት የጥናት ዘመን ያሰባሰባቸውን ቅርሶች መረጃ በአግባft ማጠናቀሩና የኪዩሬሽን ሥራ ማጠናቀቁ ተረጋግጦ ለቀጣዩ ሁለት ዓመት ሊራዘምለት ይችላል፡፡
2. የፈቃድ ዘመኑን ላጠናቀቀና በአዲስ መልክ የፈቃድ ማመልከቻ የሚያቀርብ ተመራማሪ ወይም ftድን የሚስተናገደው በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀጽ 12 እና 13 ተረጋግጦ ይሆናል፡፡

14) <u>ስለፈቃድ እድሳት</u>

1. የቅርስ ጥናትና ምርምር የፈቃድ እድሳት ጥያቄ ቀደም ሲል የተሰጠው ፈቃድ ከመጠናቀቁ ከ2 ወር በፊት በግንባር በመቅረብ፣ በፖስታ፣ በኢ-ሜይል ወይም በድህረ ገጽ በመላክ ለባለስልጣኑ መቅረብ አለበት፡፡
2. ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ፈቃድ የተሰጠው ተመራማሪ ወይም ftድን ፈቃድ ካገኘ በኋላ አቅርቦት በነበረው የጥናት ማመልከቻ መሠረት ጥናቱን በትክክል ስለማከናወኑ በሚቀርft የመስክ ሪፖርቶች ተገምግሞ ሲረጋገጥ በየዓመቱ አስፈላጊውን ክፍያ በመፈፀም የማመልከቻ ቅጹን ሞልቶ ፈቃዱ ይታደሳል፡፡
3. ከአንድ ዓመት በላይ በመስክ የሚካሄድ የቅርስ ጥናትና ምርምር ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

15) <u>ፈቃድ ስለመሰረዝ</u>

ፈቃድ ሊያሰረft የሚችሉ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ 1. ፈቃድ በተሰጠ በስድስት ወር ውስጥ ጥናቱን ካልጀመረ ፣

2. ፈቃድ የተሰጠው አካል በፈቃዱ መሠረት በአግባft እየሰራ አለመሆኑ ሲረጋገጥ፣
3. የተሰጠው ፈቃድ ከአላማው ውጭ እየተሰራበተ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
4. በቅርሶችና በመካነ ቅርሶች ላይ አደጋ ሊያመጣ የሚችል አሠራር መኖሩ ሲረጋገጥ፡፡
5. በዚህ መመሪያም ሆነ በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተጣለበትን ግዴታ በአግባft አለመወጣቱ ሲረጋገጥ፡፡

## ክፍል አራት

## ስለቅርስ አድን ፈቃድ

### 16) የቅርስ አድን ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

በቅርስ አድን የሚሠማራ ተመራማሪ ወይም ቡድን የቅርስ አድን ፍቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

1. በዘርፉ በቂ ሙያና ልምድ ያላቸውና፣ በተለያዩና ተዛማጅነት ካላቸው የሞያ ዘርፎች የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ማካተት፣
2. በቂ የፋይናንስና የሎጂስቲክ አቅም፣
3. የቅርስ ማዳንና ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን ማመላከት፣
4. በመስኩ የሰለጠኑ የባለሥልጣኑንና የቅርስ አድን ሥራው የሚካሄድበትን ክልል ባለሞያዎችን በሥራው ላይ ማሳተፍ፣
5. ሥራው የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበትን የጊዜ ገደብ የሚገልፅ፣
6. ቡድኑ ከመስክ ለሚያሰባስባቸው ቅርሶች በቂ እና ደረጃውን የጠበቀ ማከማቻ ካቢኔቶችና መደርደሪያዎችን ማሟላት የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡

### 17) የቅርስ አድን ፈቃድ ግምገማና ፈቃድ አሰጣጥ

1. ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 16 የተቀመጡትን መስፈርቶችን መሠረት በማድግ ገምግሞ ውጤቱን ለአመልካቹ ያሳውቃል፡፡
2. ለግምገማ የቀረበ ማመልከቻ ያልተሟላ ሆኖ ከተገኘ ጥያቄውን ላቀረበው ተመራማሪ ወይም ቡድን መሪ መጠይቁን አሟልቶ ወይም አስተካክሎ እንዲያቀርብ በባለስልጣኑ በኩል ይገለጽለታል፡፡ ምላሽ በተሰጠው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መጠይቁን አሟልቶ ካላቀረበ ጥያቄው ይሰረዛል፡፡
3. የቅርስ አድን ፈቃድ የአመልካቹን ስም፣የጥናትና ምርምር ቡድኑ ስም፣ የጥናቱ ርዕስ፣ ፈቃድ የተጠየቀበትና የተሰጠበትን ቀን፣ ፈቃዱ የተሰጠበትን የቅርስ አድን ፈቃድ መስክ፣ የቅርስ አድን የሚካሄድበትን ቦታ ፣ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣ ፈቃዱን የሰጠው አካል ስም ፊርማና ማህተም ይኖረዋል፡፡
4. ፍቃድን ማደስንና መሰረዝን አስመልክቶ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 14 እና 15 የተቀመጡት በቅርስ አድን ፍቃድ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

# ክፍል
# አምስት

## የተመራማሪዎችና የﬁድን መብትና ግዴታዎች

### 18) ተመራማሪ ወይም የﬁድን መብቶች

ማንኛውም ﬁድን ወይም ተመራማሪ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡፡

1. አንድ ኢትዮጵያዊ የﬁድን መሪ ከሆነ ከሚመራው የጥናት ﬁድን በተጨማሪ በሌሎች ሁለት የጥናትና ምርምር ﬁድኖች ውስጥ በአባልነት መሳተፍ ይችላል፡፡ የﬁድን መሪ ካልሆነ ግን ለነበረበት ﬁድን መሪ ተሳትፎውን በማሳወቅ በሦስት የጥናት ﬁድኖች በአባልነት ሊሳተፍ ይችላል፡፡
2. አንድ የውጭ ዜጋ የﬁድን መሪ ከሆነ በአንድ ተጨማሪ ﬁድን ውስጥ በአባልነት መሳተፍ ይችላል፡፡ የጥናትና ምርምር ﬁድን መሪ ካልሆነ ግን በሁለት ﬁድኖች በአባልነት ሊሳተፍ ይችላል፡፡ የተለየ የቴክኒክ ሙያ ያላቸው ባለሙያዎችን በተመለከተ ግን በባለሥልጣኑ ታይቶ ይፈቀድላቸዋል፡፡
3. አንድ ተመራማሪ ወይም ﬁድን በተሰጠው የጥናት ፈቃድ ዘመን ውስጥ ከመስክ ባሰባሰባቸው ቅርሶች ላይ ያደረገውን የጥናት ውጤት የማሳተም ብቸኛ ባለመብት ይሆናል፡፡
4. ተመራማሪው ወይም ﬁድኑ በተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶች የጥናት ፈቃድ እድሳት ሳያደርግ ቢቀር ባለሥልጣኑ ለአንድ ዓመት ጊዜ ብቻ የተሰጠውን የጥናት ቦታ ለሌላ አጥኚ አሳልፎ ሳይሰጥ ይቆየዋል፡፡
5. በባለሥልጣኑ የጥናት ፈቃድ ተሰጥቶት የፈቃድ ዘመኑን ያላጠናቀቀ ተመራማሪ ወይም ﬁድን ለጥናት በተፈቀደለት መካነ ቅርስም ሆነ ከመስክ ባሰባሰባቸው ቅርሶች ላይ ካለ ተመራማሪው ወይም ﬁድኑ ዕውቅናና ፈቃድ በሦስተኛ ወገን ምንም ዓይነት ጥናትና ምርምር እንዳይካሄድበት ይደረጋል፡፡

### 19) የተመራማሪው ወይም የﬁድኑ ግዴታዎች

ማንኛውም ተመራማሪ ወይም ﬁድን የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡፡

1. የጥናት ፈቃድ ተሰጥቶት የመስክ ሥራውን ፍቃዱ ከተሰጠው ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ ጥናቱን የመጀመር፤
2. ለጥናትና ምርምር ወደ መስክ ሲንቀሳቀስ የባለሥልጣኑንና ጥናቱ የሚካሄድበትን ክልል

**ተወካይ ይዞ የመሄድ ፡**

3. ለባለሥልጣኑንና ጥናቱ ከሚካሄድበት ክልል ለሚወከለው ሰውና ለሌሎቹ ኢትዮጵያውያን የጥናትና ምርምር ftድን አባላት የ24 ሰዓት የመድን ዋስትና የመግባት፤
4. በአንድ የፈቃድ ዘመን ውስጥ ከባለሥልጣኑ ወይም ከቢሮው ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የሥልጠና መመሪያ መሠረት የሚመደብለትን አንድ የቅርስ ባለሙያ በረዥም ጊዜ ትምህርት የማሰልጠን፤
5. ጥናቱ በሚካሄድበት አካባቢ የሚኖሩ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ወግ፣ ባህልና እምነት የማክበር፤
6. ከባለስልጣኑ ተወካይና ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ያለው የዕለት ተዕለት የሥራ ግንኙነት ሥነ ምግባርን የተላበሰና ከበሬታ የተሞላው እንዲሆን የማድረግ፤
7. በጥናትና ምርምር ማመልከቻ ስማቸው ያልተጠቀሱ አባላትን ባለሥልጣኑ ሳያውቀውና በጽሑፍ ሳይፈቀድ በጥናቱ ውስጥ ያለማሳተፍ፤
8. በቅርሶችና በመካነ ቅርሶች ላይ አደጋ ሊያመጣ ከሚችል አሠራር የመታቀብ፤
9. እንዲያጠና በተፈቀደለት ቦታ ላይ የጀመረውን ጥናት በተፈቀደለት ጊዜ ገደብ ውስጥ የማጠናቀቅ፤
10. በመስክ የሚከናወን የቅርስ ፍለጋ፣ የቁፋሮ ጥናት እና ቅርሶችን የማጓጓዝ ስራ ከ12 ሰዓት በኋላ ያለማካሄድ፤
11. የዓመቱን የመስክ ጥናት ካጠናቀቀ በኋላ የመስክ ሥራ ሪፖርት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የማቅረብ፤
12. በመስክ ሥራ ላይ የሚያከናውናቸውን የቁፋሮ ጥናት ሥራዎች አስመልክቶ በየዓመቱ ከሚያቀርባቸው ሪፖርቶች በተጨማሪ የቁፋሮውን ሂደት የሚያመላክት ፕላንና ቅርሶች እንዴት እንደተገኙ የሚይሳይ ሙሉ ዘገባ ቁፋሮው ከተጠናቀቀ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አጠናቅሮ ለባለሥልጣኑ የማቅረብ፤
13. የጥናትና ምርምር ፈቃድ ዘመኑ ሥራ ሲጠናቀቅ ከሚቀርበው የመጨረሻ የሥራ ሪፖርት ጋር ምርምር የተደረገባቸውን እና ዋና ዋና የግኝት ቦታዎችን የሚያመላክቱ የአየር ፎቶግራፎች፣ የቶፖግራፊክ ካርታዎችና የጂፒኤስ መረጃዎች በማካተት ለባለሥልጣኑ የማቅረብ፤
14. የቁፋሮ ጥናት የተካሄደባቸውን ቦታዎች ለቀጣይ ጥናት የማመቻቸት እንዲሁም የቁፋሮ ጥናት የተጠናቀቀባቸውን ቦታዎች ቀድሞ ወደነበሩበት ሁኔታ የመመለስ፤
15. ከመስክ የሚያገኛቸውን ቅርሶች ተንከባክቦና በሥርዓት መዝግቦ በቂና ደረጃቸውን የጠበቁ ማከማቻ ቁሳቁሶችን አሟልቶ የማስቀመጥ፤
16. ከመስክ የተሰበሰft ቅሪተ አካላትና ሌሎችንም ቅርሶች በአግባft አጽድቶና አዘጋጅቶ ለቀጣይ ጥናት በሚያመች መልኩ የማዘጋጀት፤

17. የግብረ ሕንፃዎች ፍርስራሽ፣ ቅሪቶቻቸው የማይንቀሳቀሱ ቅርሶችና ትክል ሐውልቶችን ያለማንቀሳቀስ፤

18. ለመካነ ቅርሶች፣ እንዲሁም ለሚገኙ ቅርሶች ሳይንሳዊ ይዘት ያለው ኢትዮጵያዊና የተገኘበትን ክልል አመላካች የሆነ ሥያሜ የመስጠት፤

19. ለጥናቱ የሚያስፈልጉ የቅርስ ናሙናዎችን ከሀገር ከማስወጣቱ በፊት የሚኒስቴሩን ፈቃድ የማግኘት፤

20. በመስክ ጥናትና ምርምር ወቅት በተገኙ ቅርሶች ላይ በሌላ አካል ጋዜጣዊ መግለጫ

/ፕሬስ ሪሊዝ/ ከመስጠቱ በፊት በቅድሚያ በባለሥልጣኑ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰጥ የማድረግ፤

21. ካሳተማቸው የጥናት ውጤቶች አምስት ኦሪጅናል ቅጂዎችን ለባለሥልጣኑ የመስጠት፤

22. ለባለሥልጣኑ የሚቀርft ሪፖርቶች፣ የጥናት ዶክመንቶችና የህትመት ውጤቶች በእንግሊዝኛ ያልተዘጋጁ ከሆነ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ አስተርጉሞ የማቅረብ፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>በመስክ ላይ የሚደረግ የቅርስ ጥናትና ምርምር ስልጠና</u>

20) <u>*በመስክ ላይ የሚደረግ የቅርስ ጥናትና ምርምር ሥልጠና ማመልከቻ ይዘት-*</u>

1. በመስክ ላይ ሥልጠና የሚሰጡ አሰልጣኝ መምህራን ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣

2. የሠልጣኝ ተማሪዎች ብዛትና የስም ዝርዝር እንዲሁም የትምህርት ደረጃ፣

3. አሰልጣኞቹየሠለጠኑበት የሙያ ዘርፍና የትምህርት ደረጃቸውን የሚያመላክት ማስረጃ ኮፒ፣

4. የአሠልጣኝ መምህራንና የተማሪዎች የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ማስረጃ፣

5. አሠልጣኝ መምህራኑ የሚሠሩበትን ተቋም ስምና ሙሉ አድራሻና የተቋሙን የድጋፍ ደብዳቤ፣

6. ስለ መምህራኑ ምስክርነት ሊሰጡ የሚችሉና ሥልጠናው በሚካሄድበት ዘርፍ በምርምር ሥራዎቻቸው የታወቁ ሦስት ባለሙያዎች ስምና ሙሉ አድራሻ፣

7. የመስክ ላይ ሥልጠና የሚሰጥባቸው የትምህርት መስኮች፣

8. የመስክ ላይ ሥልጠናው የሚከናወንበት ጊዜ /ቀን፣ ወርና ዓመት ምህረት/፣

9. ሥልጠናው የሚሰጥበት ክልል፣ ዞንና ወረዳ፣

10. ሥልጠናው የሚሰጥበት ቦታ ልዩ መጠሪያ፣

11. ሥልጠናው የሚሰጥባቸው ዘዴዎች፣

12. ሥልጠናውን ለማካሄድ በመስክ የሚገለገልባቸውን ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች እንዲሁም በላብራቶሪዎች የሚጠቀምባቸውን የመማሪያ ዓይነት፣ ብዛትና አጠቃቀም፣

13. ሥልጠናውን ለማካሄድ የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠንና ምንጭ፣

14. ሥልጠናውን ለማካሄድ የገንዘብ ድጋፍ የተጠየቀበት ኘሮፖዛል ኮፒ፣

15. ከመስክ ሠልጣኝ ተማሪዎች የተገኘ የገንዘብ መጠንና ዓይነት፣

16. የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጠው ድርጅት /ተቋም/ ገንዘቡን መስጠቱን ወይም ለመስጠት ቃል መግባቱንና የሚሰጥበትን የገንዘብ ዓይነት (currency) መጠን እንዲሁም ለምን ያህል ጊዜ ለመስጠት እንደተስማማ የሚያረጋግጥ ማስረጃ /ደብዳቤ/ ማቅረብ፣

17. በመስክ ላይ ሥልጠና ለማካሄድ የሚቀርብ ጥያቄ መገምገሚያ ነጥቦች በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1-10 በተጠቀሰው መሠረት ይሆናል፡፡

21) <u>በመስክ ሥልጠና ለሚሳተፉ የተቀመጡ ግዴታዎች</u>

1. በአንቀጽ 19 የተጠቀሱት የተመራማሪዎች ግዴታ በቡድን መሪውና በአሠልጣኝ መምህራን ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

2. በአንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 6፣ 7፣ 9 እና 18 ላይ የተጠቀሱት ግዴታዎች በሰልጣኝ ተማሪዎች ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም ሠልጣኝ ተማሪዎች ማንኛውንም ቅርስም ሆነ የቅርስ ናሙና ከሀገር ለማስወጣት አይፈቀድላቸውም፡፡

3. በመስክ ከሚሰለጥኑት ተማሪዎች ከ20% ያላነሱ ኢትዮጵያውያንን የሚያሳትፍ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ሆኖም የሰልጣኞቹ ቁጥር ከ5 በታች ከሆነ ቢያንስ ከእነዚህ ሠልጣኞች መካከል አንዱ ሰልጣኝ ኢትዮጵያዊ ይሆናል፡፡ በዚህ ሥልጠና የመስክ ትምህርቱ ለሚካሄድበት ክልል ተሳታፊዎች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

4. አሠልጣኙ በሥልጠናው ለሚሳተፉ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች መጓጓዣ፣ ምግብ፣ መኝታና የመድን ዋስትና ወጪ ይሸፍናል፡፡

5. ሥልጠናው የሚካሄደው ቀደም ሲል በተመራማሪዎች በተያዘና ጥናትና ምርምር በሚካሄድበት መካነ ቅርስ ላይ፣ እንዲሁም ባለሥልጣኑ ለይቶ ለአሰልጣኞች በሚሰጣቸው መካነ ቅርስ ላይ እና ተመራማሪዎቹ ራሳቸው መርጠው ፈቃድ በሚጠይቁበት ቦታ ላይ ብቻ መሆን አለበት፡፡

6. በስልጠናው ላይ ለተሳተፉ ሠልጣኞች ስልጠናው ሲጠናቀቅ የምሥክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

7. ከባለሥልጣኑ ጋር በሚደረገው ስምምነት መሠረት ተገልጋዮቹ ተገቢውን ክፍያ መፈጸም አለባቸው፡፡

## ክፍል ስምንት

## ተግባርና ኃላፊነት

22) **የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት**

1. ለቅርስ ፍለጋ ግኝት ጥናትና ምርምር የሚቀርft ማመልከቻዎች በተሟላ ሁኔታ ሲቀርft ፈቃድ ይሰጣል፡፡
2. የጥናትና ምርምር ሥራዎች በሀገሪቱ ሕግ መሠረት መካሄዳቸውን ያረጋግጣል፡፡
3. የመጀመሪያው የሦስት ዓመት የጥናት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ለተጨማሪ የሁለት ዓመት የጥናት ፈቃድ ዕድሳት ሲጠየቅ የተመራማሪውን የሚቀርft የመሥክ ሥራ ሪፖርቶችና የጥናት ውጤቶች እንዲሁም የባለስልጣኑ ተወካይ የሚያቀርበውን ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. በመስክ ሥራ ወቅት በክልል ቢሮዎች፣ በባለስልጣኑ ተወካይ ወይም በተመራማሪዎች በሚቀርft ሪፖርቶች ውስጥ የተመለከቱ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን፣ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን እንዲሁም የመመሪያ ጥሰቶችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
5. በመስክ ሥልጠና የሚወስዱ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎችን ከሀገር ውስጥ የትምህርት ተቋማት፣ ከክልል ቢሮዎችና ከባለስልጣኑ ባለሙያዎች መካከል ይመርጣል፡፡
6. ለጥናትና ምርምር የሚሰጠው ቦታ ቀደም ሲል ለሌሎች ተመራማሪዎች የተሰጡ የጥናት ቦታዎችን የማይነካ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
7. በሀገሪቱ የሚገኙ የተመረጡ የፓሊዮአንትሮፖሎጂና የአርኪዎሎጂ መካነ ቅርስ ቦታዎችን በየጊዜው እየሰየመ ለመስክ ትምህርት ቤት አገልግሎት እንዲሰጥባቸው ያደርጋል
8. ከተመራማሪዎች ጋር በመስክ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ የሚያከናውን ባለሙያ የሠለጠነበት የትምህርት ዓይነት ከሚካሄደው የመስክ ጥናት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው መሆኑንና ከዚህ በፊት በመስክ ተመድቦ ሲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባft የተወጣና የሥነ ምግባር ጉድለት የሌለበት መሆኑን አረጋግጦ ይመድባል፡፡
9. የተመራማሪዎችን ዝርዝር የያዘ የትብብር ደብዳቤ አዘጋጅቶ ጥናቱን ለሚያካሂድበት ክልል ይልካል፡፡ እንዲሁም የውጭ ዜጋ ለሆኑ ተመራማሪዎች የፓስፖርት ቁጥራቸውንና ዜግነታቸውን በመጥቀስ የይለፍ ፈቃድ እንዲያገኙ ለሚመለከተው አካል ይጽፋል፡፡
10. ጥናትና ምርምሩ የሚደረግበት ክልልና የአካባቢው ማህበረሰብ በጥናትና ምርምር ተጠቃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡
11. በአንቀጽ 23 የተቀመጡትን የባለስልጣኑ የመስክ ተወካይ ተግባርና ኃላፊነት

ይቆጣጠራል፡፡

23) <u>በመስክ የሚካሄድ ጥናትና ምርምር ስራን የሚቆጣጠር ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የመስክ ሥራው ባለሥልጣኑ በፈቀደው መሠረት የመንግሥትን ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ተከትሎ መፈጸሙን ያረጋግጣል፡፡
2. ጥናት ለሚካሄድበት ክልል ቢሮ እና ለሚመለከታቸው አካላት የሚጻፉ ደብዳቤዎችን መስክ ከመወጣቱ በፊት ተከታትሎ ያስፈጽማል፡፡ የተፈቀደውን የጥናት ቦታ የሚያሳዩ ካርታዎችና አስፈላጊ መረጃዎችን ይይዛል፡፡ የጥናት ቦታው በተፈቀደው መሠረት መሆኑን አይቶ ያረጋግጣል፡፡
3. የመስክ ሥራው ከመጀመሩ በፊት ከftድን መሪው ጋር ሆኖ ስለሥራው ዓላማ የሚገልጽ የባለሥልጣኑን ደብዳቤ ጥናቱ ለሚካሄድበት ክልል ወይም አግባብነት ላለው የመንግሥት አካል ያቀርባል፤ በመስክ ሥራ ወቅትም አስተዳደራዊ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡
4. በመስክ ሥራ ወቅት ተመራማሪዎች ከአካባቢው ሕብረተሰብና ከአመራር አካላት ጋር ለሚኖራቸው ግንኙነት በአገናኝነት ይሰራል፡፡
5. የመስክ ጥናት አጥኚው ባቀረበውና ተገምግሞ በፀደቀው የጥናት ስልት መሠረት መካሄዱን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ ለባለስልጣኑም ያሳውቃል፡፡
6. በመስክ ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ አጥኚዎች የሙያው ስነምግባር በሚፈቅደው መሠረት ጥናታቸውን እያካሄዱ መሆኑን ይከታተላል፤ ለባለስልጣኑም ያሳውቃል፡፡
7. በመስክ ሥራ ወቅት ችግሮች ሲከሰቱ በአካባቢው ከሚገኙ የመንግሥት አካላት ጋር ወዲያውኑ ግንኙነት በማድረግ ችግሩ መፍትሔ የሚያገኝበትን መንገድ ይፈልጋል፣ ከአቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ በአፋጣኝ ለባለስልጣኑ ያሳውቃል፡፡
8. በመስክ ሥራ ወቅት የተገኙ ግኝቶች በሙሉ ወደ ባለሥልጣኑ መግባታቸውን በማረጋገጥ ለግኝቶቹ ዝርዝር ካታሎግ ከተዘጋጀ በኋላ አመሳክሮ ለባለስልጣኑ ያረካክባል፡፡
9. የቅርስና የጂኦሎጂ ናሙናዎች ከመስክ ላይ ሲወስዱ ይከታተላል፡፡ ከመስክ ተሰብስበውና ታሽገው ወደ ባለስልጣኑ የሚመጡና በላቦራቶሪ ውስጥ ብቻ ተከፍተው ጥናት ለሚካሄድባቸው የጂኦሎጂ ናሙናዎች ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡
10. ከመስክ በተመለሰ በአምስት ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው የመስክ ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማት መሠረት የመስክ ሥራ ሪፖርት በሦስት ኮፒ አዘጋጅቶ ለባለስልጣኑ ያቀርባል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለ ንብረቶች አገባብ፣ አያያዝና አጠቃቀም

24) **ለጥናትና ምርምር ንብረቶች ስለሚገftበት ሁኔታ**

የጥናትና ምርምር መገልገያ መሣሪያዎችና ንብረቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገftት በሀገሪቱ ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

25) **ስለጥናትና ምርምር ንብረቶች አያያዝ**

1. በጥናትና ምርምር ስም በባለሥልጣኑ አማካኝነት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገftት ንብረቶች አያያዝ የመንግሥትን ህግና ደንብ ተከትሎ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀስ 1 መሠረት አጥኚውና ባለሥልጣኑ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገft የጥናትና ምርምር መሣሪያዎች እንዳይበላሹና ጉዳት እንዳይደርስባቸው ተገቢውን እንክብካቤ ያደርጋሉ፤ ከተበላሹም ያሰራሉ፡፡
3. በጥናትና ምርምር ስም የሚገft መሣሪያዎች ዓመቱን ሙሉ የሚሸፍን የመድን ዋስትና በአጥኚው ወይም በftድኑ ይገባላቸዋል፡፡
4. ለመስክ ጥናትና ምርምር አገልግሎት የሚውሉት ተሽከርካሪዎች የኪራይ ወይም የጥናትና ምርምር ንብረት ተብለው የተመዘገft ተሽከርካሪዎች ብቻ መሆን አለባቸው፡፡

## ክፍል አሥር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

26) **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ በማስፈጸም ረገድ የመተባበር ግዴታ

አለበት፡፡ 27) **ቅጣት**

ይህንን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡

28) **የተሻረ መመሪያ**

በአርኪዎሎጂና አንትሮፖሎጂ መስክ ስለሚካሄድ ጥናትና ምርምር ሐምሌ 12/1992 የወጣው መመሪያ (እንደተሻሻለ) በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

29) ***የመሸጋገሪያ ድንጋጌ***

*ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የጥናትና ምርምር ፈቃድ ተሰጥቷቸው ጥናታቸውን የጀመሩ ተመራማሪዎች ወይም ቡድኖች መመሪያው ተግባራዊ ከሆነበት ቀን ጀምሮ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ጥናታቸውን መቀጠል ይችላሉ፡፡*

30) ***ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች***

*ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በመመሪው በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡*

31) ***መመሪያውን ስለማሻሻል***

*ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያሊያሻሽለው ይችላል፡፡*

32) ***መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ***

*ይህ መመሪያ ከታህሣሥ* 15 *ቀን* 2006 *ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡*